

የማቴዎስ ፩ ሴቶች

# ቤርሳቤህ

የጥናት መምሪያ

Selah
PAUSE • REFLECT

# መግቢያ

በማቴዎስ ፩ ውስጥ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የዘር ሐረግ ውስጥ የአምስት ሴቶችን ስም እናያለን። ለብዙዎቻችን የዘር ሐረግ መቁጠር ከመጽሐፍ ቅዱስ ንባባችን አብልጠን የምንወደው አካል ላይሆን ይችላል። አንዳንዶቻችን ከነጭራሹ ልንዘለው እንችላለን። ሆኖም፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተዘረዘሩት በእያንዳንዱ የዘር ሐረጎች ውስጥ ትኩረትን የሚስቡ አስደናቂ ነገሮችን እናያለን፣ ማቴዎስ ፩ም እንዲሁ ነው።

የሴቶች ወይም የእናቶች ስም በአይሁድ የዘር ሐረግ ውስጥ በተለምዶ አይጠቀሱም። በእውነቱ በአይሁድ ታሪክ ዝና የነበራቸውን ትውልዶች ብቻ በመጥቀስ፣ ሌሎችን በመዝለል የዘር ሐረጎችን በአጭሩ የሚጽፉ ሰዎች ስለነበሩ፣ በዘር ሐረግ ውስጥ መጠቀስ ራሱ በጣም ትልቅ ክብር ነበር። ይህንን ስናስብ እነዚህ አምስት ሴቶች ማለትም ትዕማር፣ ረዓብ፣ ሩት፣ ቤርሳቤህ እና የኢየሱስ እናት ማርያምን ማቴዎስ መጥቀሱ በእርግጥ ሊያስደንቀን ይጀምራል።

እነዚህ አምስት ሴቶች ሕይወታቸው ሲጠና ስለ አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ስለ ወንጌል፣ እና ስለ እለት ተእለት ሕይወት የሚነግረን ነገር አለ።

© 2020 by Selah Ministries

Published by Selah Ministries
P.O. Box 479, Addis Ababa, Ethiopia

Published in Addis Ababa, Ethiopia
All rights reserved. No part of this publication may be reproduced in any form without permission from the publisher, except in the case of brief quotations embodied in other works or reviews.

All Scripture quotations are from the NASV Amharic Bible (Holy Bible, New Amharic Standard Version (Addisu Medebegna Tirgum)) Copyright © 2001 by Biblica, Inc.®
All rights reserved worldwide.

Illustrations
Front cover: Yikunoamlak Ayalew
Back cover: Ammanuel Anbessie

# ስለ ጥናት መምሪያው

የእግዚአብሔርን ቃል ለመረዳት ስንፈልግ መንፈስ ቅዱስ ዋና አስተማሪያችን መሆኑን መዘንጋት የለብንም። ኢየሱስ “መንፈስ ቅዱስ ሁሉን ነገር ያስተምራችኋል፤ እኔ የነገርኋችሁንም ሁሉ ያሳስባችኋል” ይለናል (ዮሐንስ 14፥26)። በጥናታችን ጊዜ መንፈስ ቅዱስ እንዲያስተምረን፣ እንዲለውጠን ከመጠየቅ ባሻገር የሚከተሉትን ይዘው መዘጋጀት ጠቃሚ  ነው ብለን እናስባለን።

- መጽሐፍ ቅዱስ
- ማስታወሻ ደብተር (ሐሳብዎን ለማስፈሪያ ቦታ ስላለው ይህንን መምሪያ አትመው በማውጣት መጠቀም ይችላሉ)
- በመጽሐፍ ቅዱስዎ ወይም በማስታወሻዎ ውስጥ ለመጻፍ ቀለም ያላቸው እስኪብርቶዎች ወይም እርሳሶች

በዚህ ጥናት ውስጥ ሁሉ ራስዎን እነዚህን ጥያቄዎች እየጠየቁ ይሂዱ፥

- ይህ ክፍል ስለ እግዚአብሔር ልብ፣ መንገዶች፣ እና ባሕርይ ምን ይነግረኛል?
- ይህ ክፍል ወደ ኢየሱስ እና ወደ ወንጌል እንዴት ይጠቁማል?
- ልከተለው ወይም ላስወግደው የሚገባ ምሳሌ አለ? ከሆነስ፣ ምን ዓይነት ለውጥ ወይም ምላሽ መስጠት አለብኝ?

ተጓዳኙን የጥናት ቪዲዮ መመልከት ጠቃሚ ሆኖ ሊያገኙት ይችላሉ። ቪዲዮውን ከዚህ በታች ያለውን ምስል በመንካት ወይም በድህረ-ገፃችን www.selahethiopia.org/bathsheba ያገኙታል።



# 2ኛ ሳሙኤል 11፥1-5

ነገሥታት ለጦርነት በሚወጡበት፣ በጸደይ ወራት ዳዊት ኢዮአብን ከንጉሡ ሰዎችና ከመላው የእስራኤል ሰራዊት ጋር አዘመተው፤ እነርሱም አሞናውያንን አጠፉ፤ ረባት የተባለችውንም ከተማ ከበቡ፤ በዚህ ጊዜ ግን ዳዊት በኢየሩሳሌም ቀርቶ ነበር። አንድ ቀን ማታ፣ ዳዊት ከዐልጋው ተነሥቶ በቤተ መንግሥቱ ሰገነት ወዲያና ወዲህ ይመላለስ ነበር፤ ከሰገነቱ ላይ እንዳለም፣ አንዲት ሴት ገላዋን ስትታጠብ አየ፤ ሴቲቱም እጅግ በጣም ውብ ነበረች።

ዳዊትም ሰው ልኮ ስለ ሴቲቱ አጠያየቀ። ሰውየውም፣ “ይህች የኤልያብ ልጅ፣ የኬጢያዊው የኦርዮ ሚስት ቤርሳቤህ አይደለችምን?” አለ። ከዚያም ዳዊት መልእክተኞች ልኮ አስመጣት፤ እርሱ ወዳለበት ገባች፤ አብሮአትም ተኛ። በዚህም ጊዜ ወርሐዊ የመንጻት ጊዜዋን ፈጽማ ነበር። ከዚያም ተመልሳ ወደ ቤቷ ሄደች። ሴቲቱ ፀነሰች፤ ለዳዊትም፣ “አርግዣለሁ” ብላ ላከችበት።

# ቤርሳቤህ

- 2ኛ ሳሙኤል 11፥1-5ን እናንብብ። ዳዊት በዚህ ጊዜ የት መሆን ነበረበት?

- ዳዊት በጣሪያው ላይ ሲንጎራደድ ለራሱ ወይም ለሌሎች ችግር ሊፈጥር እየፈለገ ይመስላል? ምሳሌ 17፥24 እንደሚገልጸው መሰላቸት ወይም በዕለት ተዕለት ሕይወት መደበር ከእግዚአብሔር ቤት ደህንነት ባሻገር የሚያስደስቱንን ወይም የሚያነሳሱንን ነገሮች  እንድንፈልግ ሊያረገን ይችላል።

- በ 2ኛ ሳሙኤል 11፥3 ላይ እንደምናነበው፣ ዳዊት የላካቸው ሰዎች ስለ ውብ ጎረቤቱ አስፈላጊ መረጃ ይዘው ወደ ቤተመንግስት ተመለሱ። ዳዊት ካሰበው ድርጊት፣ በልቡ ከመጣው ፍላጎት ሊያስቆመው የሚችሉ ቢያንስ ሁለት ነገሮችን ለዳዊት ነገሩት። ምን አሉት?

- የዳዊት ኀጢአቶች ግልጽ ናቸው። ግን ስለ ቤርሳቤህ ሀጢያትስ ምን ማለት ይቻላል? ተጠቂ ወይስ አሳሳች ነበረች? ሮሜ 7፥18-19 እና ገላትያ 5፥17 የቤርሳቤህን እርስ በእርሳቸው የሚጋጩ ፍላጎቶችን እንዴት ሊገልጹ ይችላሉ?

- እኛ ቤርሳቤህን ብንሆን ኖሮ፣ በዚህ በፀደይ ምሽት ወደ ሀብታም ንጉስ ቤተመንግስት ብንወሰድ ለዳዊት ግብዛ እምቢ እንላለን? ግብዛውን ለመቀበል ፈታኝ የሚያረግብን ምንድን ነው፣ ቀላልስ የሚያረገው ነገር አለ? መጥፎ ለማድረግ ብንመርጥም እንኳ የእግዚአብሔር ቃል የሚገርም ተስፋን ይሰጣል። እነዚህ ቁጥሮች ስለ ኀጢአታችን እና ስለ እግዚአብሔር ጸጋ ምን ይነግሩናል፤ ኤፌሶን 1፥7፣ ሮሜ 5፥8 እና 1ኛ ጢሞቴዎስ 1፥15?

- በ 2ኛ ሳሙኤል 11፥5 ቤርሳቤህ በመጨረሻ ስትናገር ምን ትላለች?

- ቤርሳቤህ እንደ አመንዝራ ምን ዓይነት መዘዞች አጋጥሟት ሊሆን ይችላል?

- በ 2ኛ ሳሙኤል 11፥6-7 ላይ እንደምናነበው የዳዊት ድርጊት ብዙ ያስከተላው መዘዞቶች ነበሩት። ዳዊት ዕቅዶቹን ሲያወጣ እና ሲያስቀምጥ የእግዚአብሔርን ምክር ጠይቋል? እቅድ ማውጣትን በተመለከተ ምሳሌ 16፥3 ምን ያሳያል? ለምን ዳዊት እንዲህ ዓይነቱን ጥበብ ችላ ያለ ይመስለናል?

- 2ኛ ሳሙኤል 12፥1-4ን አናንብብ። ቤርሳቤህ በናታን ምሳሌ ውስጥ እንዴት ተገለጠች? በጉዳዩ ላይ ስላላት ተባባሪነት ምን ያሳያል?

- በስተ መጨረሻ ስለ ቤርሳቤህ ስናስብ፣ በ 2ኛ ሳሙኤል 12፥24 ላይ እንደምናነበው ለዳዊት ያላት ፍቅር፣ ዳዊትም ለእሷ ያለው ፍቅር የጨመረ ይመስላል። እናም፣ በ 1ኛ ነገሥት 1፥28-31 ውስጥ በዳዊት ሕይወት መገባደጃ ላይ የተወደደች ሚስት ሆና ትጠቀሳለች። ከአምላክ ጋር ያላት ዝምድና እንደገና እንደተመለሰ ወይም እንደታደሰ ምን ማረጋገጫ አለ?

# የአሰላስሎት ጥያቄዎች

በማቴዎስ 1፥1 ላይ ኢየሱስ “የዳዊት ልጅ” ተብሎ መጠራቱን ይታወሳል፣ በማቴዎስ 1፥6 ደግሞ ንጉስ ዳዊት በክርስቶስ የዘር ሐረግ የት እንደተጠቀሰ እናያለን። ይህ ከወንጌላት ውስጥ ያለው ክፍል ዳዊትና ቤርሳቤህ ብቻ ሳይሆኑ በእግዚአብሔር ይቅር የተባሉ፣ እኛም ደግሞ ይቅር የምንባል እንደሆንን እንዴት ያረጋግጥልናል?

እስቲ እውነቱን እናውራ፤ ዓይኖቻችን ወደ አጉል ነገር ለመማተር ተፈትነን እናውቃለን? በዚህ ሁኔታ ውስጥ ምን አደረግን? ያዕቆብ 1፥13-14 እና 1ኛ ዮሐንስ 2፥16 ስለ ፈተና ምን ይነግሩናል?

እግዚአብሔር ለኀጢአታችን ይቅርታን ሊሰጠን ይችላል፤ ኀጢአታችንነ ተከትለው የሚመጡ ውጤቶችን ወይም መዘዞችን እንድንጋፈጥ ፀጋን ይሰጠናል። በሕይወታችን ይሄን እንዴት አይተነዋል? እግዚአብሔር እኛ በሕይወታችን አበላሽነው ወይም እንዳይመለስ በኀጢአታችን አጨቀየነው ያልነውን ነገር እንዴት ሲጠቀም እናያለን?

# አስተያየቶች



Selah
PAUSE • REFLECT

# ጥበብ

የእግዚአብሔር ሕግ ፍጹም ነው፤ ነፍስንም መልሶ ያለመልማል፤ የእግዚአብሔር ሥርዐት የታመነ ነው፤ አላዋቂውን ጥበበኛ ያደርጋል።

መዝሙር 19:7

**ሁሉንም የሴላ ጥበብ ጥናቶች ለማግኘት**

www.selahethiopia.org/studies